# ከሁሉም በላይ የሀገርንና የህዝብን ደህንነትና አንድነት ይቅደም!!

## በዲያስፓራ የዓረና መድረክ ደጋፊዎች የተሰጠ የጋራ አቋም መግለጫ

E-mail:- arenamedrekd@gmail.com

በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ በመሄድ ላይ የሚገኘው ህዝባዊ ተቃውሞና ብሶት በማስመልከት በውጭ ዓለም የሚኖሩ የዓረና መድረክ ደጋፊዎች ከተለያዩ ቦታዎች ሰሞኑን ባደረጉት አስቸኳይ የቴሌ ኮንፈረስ ውይይት የሚከተለውን ባለስምንት ነጥብ የጋራ የአቋም መግለጫ ለመላ ኢትዮጵያውያን አስተላልፏል።

ዓይናቸውን በፍቅረ ንዋይና በስልጣን ጥምነት የተሰወሩ አምባ ገነኖች የትም ይብቀሉ የትም ተመሳሳይ ባህርይ አላቸው። ዙሪያቸውን በወታደራዊ ሐይል ተከቦ ሲያዩት ዓለምን በመዳፋቸው ውስጥ ያስገቡት ይመስላቸውና ልባቸውን በትዕቢትና በትምክህት ስለሚሞላ ነፃነትና ፍትሕ ከሌለ ነገ ፈራሽ መሆኑን ከታሪክ አይማሩም። ሰብኣዊ ርህራሄና የይቅርታ መንፈስ የላቸውም። የህልውናቸውን መሰረት <u>ሕብረተሰቡን በዘር፣ በጥቅምና በሀይማኖት ለያይተህ ግዛ</u> የሚል ስለሆነ የህዝቡን ነፃ እንቅስቃሴ፣ አንድነትና መደራጀት ከጦር በላይ ይፈሩታል። ራሳቸውን ልዩ ፍጡራንና ጀግኖች አድርገው በመመልከት ከሀገርና ከሕግ በላይ በመሆን የህዝቡን ጭኾትና ህይወት የዶሮን ያህል ግምት አይሰጡትም። የዓይን ብሌየናቸው ገንዘብና ስልጣን ስለሆነ የሀገርንና የወገንን ፍቅር የላቸውም። በርስትነት በያዙት የብዙሃኑ መገናኛ አማካኝነት ነጋ ጠባ የሚያስተጋቡት መዝሙርና የጉራ ነጋሪት <u>በለው፣ ፍለጠው፣ ርግጠው፣ ቁረጠው፣ ግደለው</u> ከሚል ቀረርቶ በስተቀር የህዝቡን ብሶት የማዳመጥና አርቆ የማየት ዓቅም፣ ሞራል፣ ብቃትና ተፈጥሮ የላቸውም። ይህ በመሆኑም የህዝቡን ዓመፅ ቤተ መንግስታቸው አፋፍ ላይ ደርሶ እንደ እሳተ ጎመራ እስከሚለበልባቸው ድረስ ተቻችሎና ተከባብሮ አብሮ ከመኖር ይልቅ <u>እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል</u> በማለት እስከመጨረሻ ህልፈታቸው ድረስ መሟሟትንና መተላለቅን ይመርጣሉ። ሀገርንና ህዝብን አጥፍቶ መጥፋት ማለት ትርጉሙ ይኸው ነው።

የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስትም ከአምባ ገነናዊ ተፈጥረው በመነሳት 90 ሚሊዮኑን የኢትዮጵያ ህዝብ በማግለልና የበይ ተመልካች በማድረግ ሀገሪትዋን ጠቅልሎ በሞኖፓል እየገዛ ይገኛል። ተቃውሞ ያነሳ ዜጋ ሁሉ በአግባቡ ከማስተናገድና ዴሞክራሲያዊ መፍትሔ ከመሻት ይልቅ ልክ ትናንት ደርጋውያን በመውደቂያቸው ዋዜማ ያሳይዋቸው የነበረ የቀቢፀ ተስፋ እርምጃዎችና ፉኮራዎች ዛሬም በተመሳሳይ መልኩ የመብት ጥያቄ ያነሱትን ዜጎች ሁሉ የተለያዩ የቂጥያ ሰሞችን በመለጠፍ የሻዕቢያ ተላላኪ፣ ሽብርተኞች፣ የደርግ ስርዓት ናፋቂዎች፣ ትምክህተኞች፣ የጎዳና ነውጠኞች፣ ቦዘኔዎች፣ ነፍጠኞች፣ ወዘተ በማለት ፍትሓዊ ጥያቂያቸውን በማናናቅና በማፈን ወታደራዊ የሐይል እርምጃው ትግራይን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ሲተገበር ቆይቷል።

### የተከበርከው የትግራይ ህዝብና መላው ወገናችን

ይህ የሐይል እርምጃና የመብት ረገጣ ዛሬ በኦሮምያና በአማራ ክልሎች ብቻ የተጀመረ ሳይሆን በተለይም የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ነኝ የሚለው ህወሓት በአስር ሽዎች ሰማእታት የወደቁበትን የትግል አላማ ከህዝቡ እጅ ነጥቆ በመውሰድ ጥቂት በቤተሰብ፡ በጋብቻና በትውልድ ሐረግ የተሳሰሩትን ዘመድ አዝማድ መሪዎች ጥቅም ማስጠበቂያ በማድረግ የህዝቡንና የሰማእታቱን አደራ የበላ ድርጅት ነው። ዛሬ በትግራይ ምድር “እኔ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነኝ” ወይም ትግራዋይ ነኝ ብለህ በነፃነት ኰርተህ ለመረማመድ ቀርቶ እንደ ሰብኣዊ ፍጡር በህይወት ለመኖርም አስቸጋሪ የሆነበት ጊዜ ነው። እንደ መሪዎቹና ካድሬዎቻቸው አመለካከት ከሆነ በትግራይ የህወሓት ደጋፊ ያልሆነ የክልሉ ተወላጅ እንደ ትግራዋይ ተደርጎ ስለማይታይ ዴሞክራሲያዊ መብቱን ብቻ ሳይሆን ስብእናውን፣ ዜግነቱንና ማንነቱንም ጭምር የተነጠቀ ነው። ይህንን የህወሓት የሰብኣዊ መብት ረገጣን በመቃወም በተለያየ ጊዜ በክልሉ በተንቤን ዓቢይ ዓዲ፣ በነበለት፣ በእምባስነተይ፣ በሁለት አውላዕሎ፣ በእግሪ ሐሪባ፣ በዓዲ ረመፅ፣ በብዘትና በሌሎች ወረዳዎች ላይ የተደረጉትን የህዝቡን የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎች በወታደራዊ ሐይል ከመበተንና ከማጥቃት አልፎ ሰልፉን አስተባብሯል የተባሉትን ግማሾቹ አምልጠው ወደ ስደት ሄዷል ሌሎቹ ደግሞ የት እንደገቡ የማይታወቅ የውሃ ሽታ ሆነው ቀርቷል። ቤተሰቦቻቸውንም እንደውሻ ከያሉበት እየታደኑ ታስሯል፡ ተሰዷል፡ አሊያም ደብዛቸው ጠፍቷል። ሌላ ቀርቶ ምርጫ መጣ በተባለ ቁጥርና በዋዜማው በመላ ትግራይ እስከ አፍንጫውን የታጠቀ መደበኛ ሰራዊትን በማዝመትና አካባቢውን በጥይት ጭኾት ነጎድጓድ በማደንቆር ሻዕቢያ ባንተ ላይ ሊዘምት ተንቀሳቅሷል እያሉ ህዝቡን በማሸበርና በማስደንገጥ የምርጫ ጎሮጀውን ከህዝቡ እጅ በአፈ ሙዝ ነጥቀው በመውሰድ መቶ በመቶ አሸንፈናል ይላሉ።

ከዚህም በላይ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ጥያቄን በማንሳት በሕግ ተመዝግበው፡ የህዝቡን ልዕልና አክብረው፡ ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል አምነው፡ ሕገ መንግስቱ የፈቀደላቸውን መብት መሰረት አድርገው በመታገል ላይ በሚገኙት የዓረና ትግራይ ለሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ አባላት ላይ እየደረሰ ያለው በደል ስንመለከትም ህወሓት ምን ያህል የሰብኣዊ ፍጡር ደመኛና ባላንጣ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። በትግራይ የተለየ አመለካከት መያዝ ወይም የዓረና ትግራይ ደጋፊ መሆን ማለት እንደ ነውር ወይም እንደወንጀለኛ ስለሚያስቆጥር ከማሰር፣ ከመግደልና ከማፈን አልፈው “የዓረና አባል ለሆነ ትግራዋይ ሁሉ እሳት እንዳታስጨሩ፣ ሲሞት እንዳትቀብሩ፣ ልቅሶ እንዳትደርሱ፣ በሃዘንም ሆነ በደስታ ከነርሱ ጋር በአካል እንዳትገናኙና እንዳትቆሙ፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አግልሏቸው” የሚል ማሕበራዊና ሀይማኖታዊ ውግዘት እንዲደርስባቸው ያደርጋሉ። በመላ አባላቱ ላይ የከፈቱትን የስነ ልቦናዊ ጦርነት አልበቃ ብሏቸው በሆዳቸውና በህልውናቸው ለመቅጣት ሲባልም የስራ ዕድል እንዳያገኙ፡ ሀብት እንዳያፈሩ፡ ሌላ ቀርቶ ከለጋሽ ሀገሮች የሚመጣውን የስንዴ እርዳታም ሳይቀር እንዳይሰጣቸው ይከለከላሉ። ገበሬ ከሆነ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር እንዳያገኝ፣ የመንግስት ሰራተኛ ከሆነ ከስራው እንዲባረር፣ ተማሪ ከሆነ ተምሮ የስራ ዕድል እንዳያገኝና ከተለያዩ የትምህርት ዕድሎች

እንዲታገድ፣ ነጋዴ ከሆነ ደግሞ ንግድ ቤቱን እንዲዘጋ አሊያም ከመጠን በላይ ግብር እንዲጫንበት እየተደረገ ይገኛል:: በቤተሰብ ደረጃም ዘልቀው በመግባት ልጆቻቸው የዓረና አባል ሆነው የተገኙትን ወላጆች ይቀጣሉ:: ሚስት ወይ ባል የዓረና አባል ሆኖ ከተገኘ ሚስቱ ባልዋን እንድትፈታ በማድረግ ቤተሰብ ያፈርሳሉ ይበትናሉ:: ህዝቡን ሳይወድ በግድ አንድ ለአምስት በማደራጀት እርስ በርሱ እየተናከሰ እንዲኖር በማድረግ በተለይም የዓረና አባላትን የማጥቂያ መሳሪያ አድርገው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ:: በዚሁ አስከፊ የአፈና እርምጃ ምክንያት በተለይም ወጣቶቹ ያላቸው ምርጫ ሳይወዱ በግድ ባርነትን አሜን ብሎ ተቀብሎ መኖር ወይም ዓይኑን ጨፍኖ ወደ ስደት መፍለስ ነው:: ከዚህ በላይ ጭካኔ! አረሜንነትና በደል ምን ሊባል ይችላል:: እውነት ህወሓት የትግራይ ህዝብ ጠበቃና ነፃ አውጪ? ህሊናችሁን ይፍረደው::

ዛሬ በኦሮሞያ: በአማራና በሌሎች ቦታዎች የተነሳው ህዝባዊ እምቢተኝነትና የፍትሕ ጥያቄ በትግራይ ምድር እየተፈፀመ ካለው የሙብት ረገጣና ኢፍትሓዊ እርምጃ የተለየ አይደለም:: የኢሕአዴግ መሪዎች በተለይም ህወሓት የሁሉንም ቅራኔዎች: ጭቆናዎችና ዓፈናዎች መንሲኤ እነርሱ ራሳቸው ሆኖ ሳለ ዛሬም እንደለመዱት የማደናገሪያና የማጨበርበሪያ ተንኰላቸውን በመቀጠል የህዝቡን ጠበቃ በመምሰል በሌሎች ክልሎች የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ በትግራይ ላይ ያነጣጠረ የእልቂት ጦርነት በማስመሰል የሽብር ፕሮፓጋንዳ መርዛቸውን በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ:: ይሁን እንጂ ከመጋረጃው በስተጀርባ ያለው ተግባር ግን ሐቁ ሌላ ነው:: ህወሓት ከተፈጠረባት ቀን አንስቶ እስካሁን ድረስ ስንመለከተው በዘረጋው የዓፈናና የለያይተህ ግዛ ፖሊሲ መሰረት ትግራዋይን እየገደለ ያለው ራሱ ህወሓትና አጋሮቹ ናቸው እንጂ ሌላ ባዕድ አይደለም:: ትግራዋይን ሆን ብሎ ከኤርትራ ህዝብም ሆነ ከሌሎች አጎራባች ወንድሞቹ ጋር እሳት እየጫረ በጠላትነትና በጥርጣሬ ዓይን እንዲታይ ሌት ተቀን ጥረት እያደረገ ወገኖቻችንን ለግድያና ለቃጠሎ እንዲዳረጉ ምክንያት እየሆነ ያለው ራሱ ህወሓት እንጂ ሌላ አይደለም:: ትግራዋይን ከቤት ንብረቱንና ከየመንደሩ እየተፈናቀለ ወደ ባህር ማዶና በየቦታው እየተጣለና እየተሰደደ ያለው የህወሓትን አድልዎና አፈና የፈጠረው ጠንቅ እንጂ ሀገሩንና ህዝቡን ጠልቶ አይደለም:: ትግራዋይን በሻዕቢያ አለንጋ እየተገረፈ ከየቤቱ እየታደነና እየታፈነ መረብ ተሻግሮ ደብዛው እንዲጠፋ ምክንያት እየሆነ ያለው ራሱ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪና ጠበቃ ነኝ እያለ የሚመፃደቀው ህወሓት እንጂ ሌላ አይደለም:: እንደነ ታደሰ አብርሃንና አረጋዊ ገብረዮሐንስን የመሳሰሉት ወጣት የዓረና መሪዎች የገደለና እነ አብርሃ ደስታን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች የተለየ አመለካከት ስለያዙ ብቻ እስር ቤት አጉሮ እያሰቃየና እያሳደደ ያለው ራሱ ህወሓት እንጂ ሌላ አይደለም:: ህወሓት ራሱ ባመጣው ጣጣ ሻዕቢያ የትግራይ ህዝብን በወረረ ጊዜ ፈጥኖ ደራሽ በመሆን ከእልቂት ያዳነው ራሱ የትግራይ ህዝብን ጨምሮ ጠቅላላ ኢትዮጵያዊ እንጂ ህወሓት ብቻውን አይደለም:: በሚሊዮን የሚቆጠረው ትግራዋይ በመላ ኢትዮጵያ ሀብትንና ንብረትን መስርቶ እየኖረ ያለው ህወሓት የቸረው ሙብት ሳይሆን ለዘመናት አብሮ ተፋቅሮ የቆየና የገዛ ሀገሩ መሆኑን ስለሚያቅ ነው:: ትግራይም የትግርኛ ተናጋሪ ብቻ ሳትሆን የሌላውን ወገን አጥንት የተቀበረባት የሁሉም ኢትዮጵያዊ መሬት ናት:: ስለዚህ የትግራይ ህዝብ ጠበቃና መድህን 90 ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ በምንም መልኩ ጠላቱ ሊሆን አይችልም:: ስለዚህ በአጠቃላይ <u>ለትግራዋይ ከህወሓት በላይ ጨቋኝና አፋኝ ስርዓት የለውም ቢባል ማጋነን አይሆንም</u>::

## የተከበራችሁ ውድ ኢትጵዮያውያን በሙሉ

ከላይ የተጠቀሱትን ሐቆች እንደተጠበቀ ሆኖ በቅርቡ በኦሮሚያ፣ በአማራና በሌሎች አካባቢዎች የተደረጉትን ህዝባዊ ሰልፎች በአመዛኙ በመላ ሀገሪቱ ላይ ያሉት ችግሮች ተመሳሳይ ስለሆኑ ትግላቸው የሚደገደገፍ ነው ብለን እናምናለን:: ይሁን እንጂ እኛም ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ ቁስል ያላቸውን ጭቁን ወገኖች የትግሉን አጋር በመሆን በሙሉ ልባችንና ዓቅማችን እንዳንሳተፍ የሚያደርጉ አግላይ: ከኢትዮያዊነት ስነ ምግባርና ሃላፊነት ውጭ የሆኑትን አስጊ አዝማሚያዎችና ተግባራት ሲፈፀሙ ስናይ እጅጉን አሳዝኖናል:: የሚያሳዝነውም ድርብ ድርብርብ ጉዳት ስላለው ነው:: አንደኛ ድርጊቱ የጭቁኖች ኢትዮጵያውያንን የትግል አንድነት የሚያላላና የሚያዳክም ነው:: ሁለተኛ በየአካባቢ የተነሳውን የህዝቡን እምቢተኝና እየተከፈለ ያለውን አኩሪ መስዋእትነት መንገዱንና አቅጣጫውን በማሳሳት እንደተለመደው ተዳፍኖና ደመ ከልብ ሆኖ እንዲቀር የሚያደርግ ነው:: ሶስተኛ እነዚህ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚደረጉ ስህተቶች ዞሮ ዞሮ ተጠቃሚ የሚሆነው ፍትሕ የጠማውን ህዝብ ሳይሆን እኛን በዘርና በሀይማኖት ከፋፍለው እርስ በራሳችን አናቁረውና በታትነው በጭቁኖች ደም እነርሱ ዘላለማዊ ስልጣናቸውን አደላድለው ለመኖር የሚፈልጉ አምባ ገነን መሪዎችንና ተከታዮቻቸውን የሚያጎለብት ነው:: አራተኛ እየተፈፀመ ያለው የተዛባ ተግባርና እንቅስቃሴ በቂም በቀልና በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ<u> በዘር ማጥፋት ወንጀለኝነትንም ጭምር የሚያስጠይቅ ጥቁር የታሪክ ጠባሳ ነው</u>:: አምስተኛ ሀገርን የሚበታትን ከመሆኑም በላይ የእርስ በርስ እልቂትን የሚጋብዝ ስለሆነ በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን:: ይህንን አደገኛ አዝማሚያ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታና እንዲገታ ለማድረግም የፓለቲካ ድርጅቶች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ሲቢክ ማሕበረ ሰቦች፣ ምሁራን፣ ወጣቱ ትውልድና ጠቅላላ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ዓለም የሚኖሩት ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሰላም ትብብራቸውን እንዲያሳዩ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

እዚህ ላይ መሰመር ያለበት ዓቢይ ጉዳይ ይህ የተዛባና መንገዱን የሳተ: በጥቂት ቡድኖች አነሳሽነት እየተፈፀመ ያለው ፀረ ህዝብና ፀረ አንድነት ተግባር ጨዋውና የዋሁን የአማራና የኦሮሞ ህዝብ ተግባር ነው ብለን ፍፁም አናምንም:: ትናንትም: ዛሬም ሆነ ነገ በምንወደው በአማራውና በኦሮሞው ህዝባችን ላይ ያለንን ልባዊ ፍቅር: ፅኑ እምነትና አክብሮት ፍፁም አይለውጠውም:: ተራራን የሚያህል የጋራ ጠላት ፊት ለፊታችን ተጎልቶ እያለ ነገር ግን የጀመርነውን ትግል በዋናው ዓቢይ ጉዳይ በጋራ ጨቋኞቻችን ላይ ያነጣጠረ እንዳይሆን መንገዳችንን በማሳሳት እነሱ በሚሰጡን አጀንደ ላይ ተጠምደን ነገ ሁላችንም በእኩል የሚያስተናግድና ድምፃችንን የሚሰማ ስርዓት ሲረጋገጥ እግረ መንገዳቸውን ሊፈቱ በሚችሉ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ በማትኮር ራሳችን በራሳችን ትግላችንን የሚጎዳ ተግባር መፈፀም ማለት ለጠላቶቻችን ዱላ ማቀበል ማለት ነው የሚሆነው::

ይህን ዓይነቱ ስሜት የወለደው ስህተት ደግሞ እውነተኛ የወገንና የሀገርን ፍቅር ካላቸውና ነገ ሁሉንም ብሄር ብሄረሰቦች በእኩል የሚስተናገዱባት: ነፃነትዋንና የግዛት አንድነትዋን የተጠበቀች: አንዲት የበለፀገች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንድትረጋገጥ ከሚመኙና ከሚታገሉ ሐይሎች ይመነጫል ብለን ፍፁም አናምንም:: ምክንያቱም በሀገራችን የነበረውና አሁን ያለው ታሪካዊና ነባራዊ እውነታ የሚያረጋግጥልን አንድና አንድ

ብቻ ነው። እሱም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እውን እንድትሆንና ነፃነትዋንና ክብርዋንም ጠብቃ እስከ ዛሬ ድረስ እንድትኖር ያደረጉዋትና የመስዋእትነትን ዋጋ የከፈሉላት አንገፋና አናሳ ሳይባባሉ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች ናቸው። ስለዚህ አንዱን ዘር በማግለል ወይም በመጥላት ነገ ሁላችንም የምንመኘው ፍትሕ፡ ነፃነት፡ ዴሞክራሲና ሰላም በፍፁም ሊረጋገጥ አይችልም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርንም መኖር አትችልም። በዘር ጥላቻና በሀይማኖት ላይ የተመሰረተ ፓለቲካዊ እንቅስቃሴ ውጤት ሊኖረውና የሀገርንና የህዝብን ሉዓላዊ ክብርና አንድነት ሊያስጠብቅ እንደማይችል ሩቅ ሳንሄድ በጎሮቤቶቻችንና በሌሎች ሀገሮች እየተካሄዱ ያሉትን አውዳሚ ክስተቶች ጉልህ አብነቶች ናቸው።

በኛ እምነት ሀገር ማለት ህዝቡን ነው። ኢትዮጵያም የህዝቡን የትግል ቃል ኪዳን ውጤት ናት። በመሆኑም ህዝብዋን እየጠሉ ሀገር ወዳድ መሆንና ሀገር አለኝ ማለት አይቻልም። የሀገራችንን የአንድነት ሞሶሶ ተጠብቆ እንዲቆይ ያደረገው ዋናው ሚስጢሩም በመተማመን፡ በመከባበር፡ በመቻቻል፡ በመፈቃቀድ፡ በመረዳዳትና በመፈቃቃር ላይ የተመሰረተ የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች የአንድነት ቃል ኪዳን ነው። ከዚህ ውጭ አሁን ከደረስንበት 21ኛው የሰለጠነ ዘመንና የዓለም ህዝቦች ከጠባብ መንደራቸውን አልፈው በሁሉም መስክ በጋራ ጥቅምና በሰጥቶ መቀበል መርሕ ላይ የተመሰረተ አብሮ መኖር በጀመሩበት መዋእል ላይ እየኖርን ነገር ግን ይህን ሐቅ ማየት የተሳናቸው እንደገና እኛን ወደኋላ ወደ 16ኛው የመሳፍንት ዘመን መልሰው <u>በዘርና በህዝብ ቆጠራ ላይ የተመሰረተ ስርዓት በመትከል ትልቁን ዓሣ ትንሹን ዓሣ እየበላና እየረገጠ የሚኖርባት ኢትዮጵያ</u> እንድትሆን የሚመኙት ሐይሎች ፍፁም የማይሆንላቸው መሆኑን አውቀው በአስቸኳይ ከስህተታቸውንና ከኋላቀር ድርጊታቸውን እንዲታቀቡ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

## የተከበራችሁ ታጋይ ሐይሎችና ሲቪክ ማሕበረሰቦች

አሁን በሀገራችን ያለው ሁኔታ ለሕግ ተገዢ የሆነ መንግስትና በሕግ የሚዳኝ ሕብረተሰብ በሌለበት፣ ሓላፊነት የሚሰማው መንግስትና የአመራር ብቃት ያላቸው የፓለቲካ መሪዎች በሌሉበት፣ ህዝብና መንግስት እሳትና ጭድ ሆነው በተፋጠጥ በቆሙበት፣ በአጠቃላይ ሀገራዊ የትግል አንድነት ባልተፈጠረበትና መልክ ባልያዘበት ሁኔታ ላይ እያለን ይህ ዓይነቱ የፓለቲካ ቀውስ መከሰቱ እጅግ የሚያሳስብና ፈታኝ ጊዜ ነው። ሰው እየሞተ ነው። በሽዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን ከማንም ጊዜ በላይ እየታፈሱ እስር ቤት እየተወረወሩ ናቸው። ሰዎች በማያውቁት ጉዳይ ላይ ጥቃት እየደረሰባቸውና ቤት ንብረታቸውን እየተው እየተፈናቀሉ ናቸው። ይህን ሁሉ ተደምሮ ሲታይ የሀገርንና የህዝብን ጥያቄ መልስ የሚሰጥና መስመር የሚያስይዝ ባሌቤት በማጣት ትልቅ የአመራር ክፍተት ተፈጥሯል። ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ ደግሞ ሀገሪቱን ወደ ባሰ የፓለቲካ ቀውስና ብጥብጥ ልታመራ እንደምትችል የሚያጠያይቅ አይደለም። ስለሆነም ይህንን አስፈሪ ሁኔታና የእልቂት ድባብ ለመለወጥ ህዝብ፡ መንግስትና ሌሎች ታጋይ ሐይሎች ሚና ምን መሆን አለበት? ለሚለው ጥያቄ ትእግስት፡ ጥበብ፡ በሳል፡ ብቃት፡ የነቃና የተዋሃሃደ ጥረት የሚጠይቅ ታሪካዊ ሓላፊነት የተጣለባቸው መሆኑን በሀገሪትዋ ያለውን ሁኔታ ራሱ ተናጋሪ ነው።

የኢሕአዴግ መንግስት አሁን ያለበት ሁኔታ ስናይ የህዝቡን ድምፅ ሰምቶ ዴሞክራሲያዊ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ዓቅምና ተፈጥሮ እንደሌለው ራሱም ጭምር እያመነ ነው። ዛሬ በስልጣን ላይ ያሉት የስርዓቱን መሪዎች ብቃትና ራእይ ማነስ ብቻ ሳይሆን ለራሳቸው የግል ጥቅማቸውን በማሳደድ ላይ የተጠመዱ ስለሆኑ ስለሀገርና የህዝብ ችግር ለማሰብ ጉዳያቸውም አይደለም። በአሁኑ ጊዜ ሓላፊነት የሚሰማው የመንግስት አካል ማን ነው ብለህ ለማወቅ አስቸጋሪ የሆነበት ጊዜ ነው ያለው። የመንግስት አካላትን ስንመለከት ሁሉም የየራሱ ቡድናዊና ቤተሰባዊ መንግስት በመመስረት የየግሉን አጀንዳ ይዞ የሚሯሯጥ ነው። ህዝቡም በመንግስቱ ላይ አሜኔታ በማጣቱ በራሱ መንገድ መሄድ ጀምሯል። ሰሞኑን የኢሕአዴግ ፓሊት ቢሮ ያካሄደው አስቸኳይ ስብሰባም ገና ከጅምሩ ውጤት አልባ እንደሆነ ያወጣውን መግለጫና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ራሳቸውም ለጋዜጠኞች የሰጡትን ቃለ ምልልስ ያመላክታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የነገሩን መርዶ ኢሕአዴግ አሁንም በራሱ ጎጆ አጥር ግቢ ውስጥ እየተሽከረከረ እንደሚቀጥል ነው። እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገላለፅ መተካካት (ትራንስፎርመሽን) የሚሉትም ትርጉሙ አረጌውን ስርዓት ፓሊሱና ርእዮተ ዓለም እንዳለ ሆኖ ነባር የኢሕአዴግ አባልን በአዲስ የኢሕአዴግ አባል መተካት ማለት ነው። ስለዚህ የመልክ መቀያየር እንጂ የባህርይና ያስተሳሰብ ለውጥ አልተደረገም ሁለቱም ያው ናቸው። ይህ ዓይነቱ ንግግርና መግለጫ ደግሞ ላለፉት ሃያ ዓመታት የህዝቡን ጆሮ ያደነቆረና የሰለቸ አነጋገር ነው።

ኢሕአደግ እውነት ለለውጥ ቆርጦ የተነሳ ቢሆን ኖሮ የመርፌን ቀዳዳ ያህል የጠበበውን የፓለቲካ ምሕዳር በሩን በመክፈት በሀገራችን ጉዳይ ላይ እኛም ያገባናል የሚሉትን ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎችን ለማስተናገድና ለመሳተፍ የሚችሉበትን የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት ተግባራዊ ባደረገ ነበር። ስለዚህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመግለጫቸው የነገሩን ነገር ካለ አሁንም የህዝቡን ድምፅ ለማፈን ወታደራዊ ጡንቻቸው እንዲሚያጠናኩሩ ነው። ሌላው በፓሊት ቢሮው የወጣውን መግለጫ ያነበብነው የኢሕአዴግ መንግስትን የግለ መሪዎችን ጥቅም ማካበቻ አድርጎ መጠቀም የሰርዓቱን ዋነኛ አደጋ እንደሆነ ይጠቁማል። ይሁን እንጂ ሁሉም ባለስልጣን በየደረጃው በኪራይ ሰብሳቢነት ስኳር የተለከፈ ስለሆነ ማን በማን ላይ ደፍሮ ይዘምታል የሚል ጥያቄ ምልክት ነው። መንግስት እወስዳለሁ ያለውን እርምጃም ምናልባት ግምገማ በሚል ሰበብ ህዝቡን እርስ በርሱ ለማናከስና ትግሉን ለማቀዝቀዝ ወይም አንዳንድ ባለስልጣናትን ለመምታት ይጠቀሙበት ይሆናል እንጂ የተነሳውን አንገብጋቢና ስር የሰደደውን የህዝብ መሰረታዊ ጥያቄ የሚመልስ አይሆንም። ሁሉንም በአንድ ድርጅት የበላይነት ሞኖፓላዊ አስተሳሰብ በተጠመቁ ግለ መሪዎች መካከል ሹም ሽር በማድረግና ወንበርን በመቀያየር የሚፈታ ችግር አይኖርም። የችግሩን መንሲኤ የግለ ሰቦችን ጉዳይ ሳይሆን የስርዓቱን መበስበስና አፋኝ ፓለሲያቸውን የወለደው ችግር ነው። ስለዚህ የችግሩን ምንጭ የሆነውን የስርዓቱን ፓሊሲ ለውጥ ሳይደረግ አንድ አምባ ገነን መሪን በማባረር በሌላ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያለውን አምባ ገነን መሪ ቢተካ ነገ ተመልሶ ወደ ሌብነት መግባቱ አይቀሬ ነው። ምክንያቱም ህዝቡን የስልጣን ባለቤትነቱን ሙሉ በመሉ ሳይረጋገጥ ማለት ነፃና ገለልተኛ የሆኑትን የፍትሕ፡ የዳኝነት፡ የዴሞክራሲና የምርጫ ተቋማት እስከሌሉ ድረስ ኪራይ ሰብሳቢነትንና የስርዓቱን መበላሸት መዋጋትና መቆጣጠር አይቻልም። የኢሕአዴግ ስርዓት ባህርይም ካለፈው ልምዱን ስንመለከት ስር ነቀል የሆነ የተሃደድሶና የፓለሲ ለውጥ(reform) ማድረግ ማለት ራስህን በራስህ የመግደል (sucidal) እርምጃ አድርጎ ስለሚያየው <u>ከእባብ እንቁላል እርግብ ይወለዳል</u> ብለን አንጠብቅም።

**ውድ ኢትዮጵያውያን**

እኛ የዓረና መድረክ ደጋፊዎች ይህንን የአቋም መግለጫ እንድናወጣ የተገደድንበት ዋናው ምክንያት በሀገራችን ውስጥ የተከሰተውን የፓለቲካ ቀውስና በወገኖቻችን ላይ እያስከተለ ያለውን የህይወትና የንብረት መጥፋት አደገኛ አዝማሚያን በሚመለከት ያለንን ስጋት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ዓለም ለሚኖረው መላ ወገናችን መልእክታችንን ለማስተላለፍ ነው።

1. ሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብታችን ይከበር!! ድምፃችን ይሰማ!! በማለት ሕገ መንግስቱ የሰጣቸውን መብት ተጠቅመው በሰላም አደባባይ ወጥተው አቤት ስላሉ ብቻ ወታደራዊ እርምጃ ተወስዶባቸው በየጎዳናው የወደቁትን ወገኖቻችን የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን እንገልፃለን። የከፈላችሁትን አኩሪ መስዋእትነት ለፍትሕ፣ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የተከፈለ ዋጋ ነውና ታሪካችሁን ለዘላለም ህያው ሆኖ ይኖራል። በዚሁ አጋጣሚም ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው ለመላ ህዝባችን መፅናናትን እንመኛለን።

2. ህዝቡ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ፍርሓትን ሰብሮ አደባባይ በመውጣት ለመብቱ እያደረገ ያለው የሞት ሽረት ትግል መበረታታ አለበት ብለን ስለምናምን ድጋፋችንና የትግል አጋርነታችንን እንገልፃለን። ለወደፊትም ከዘር ጥላቻ፣ ከቂም በቀልና ከጠባብ አስተሳሰብ በፀዳ መልኩ፣ ሀገርንና የ90 ሚሊዮን ህዝብን ጉዳይ ማእከል ያደረገ፣ ሀቀኛ ኢትዮጵያዊነትንና እውነተኛ ህዝባዊ አላማን መሰረት አድርጎ በሚካሄደው የለውጥ እንቅስቃሴ ከህዝባችንና ከታጋይ ወገኖቻችንን ጎን በመሰለፍ የበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት ዝግጁነታችንን በዚሁ አጋጣሚ ለመግለፅ እንወዳለን።
3. በስልጣን ላይ ያለው የኢሕአዴግ መንግስት ለተፈጠረው ችግር መንሲኤና ተጠያቂ ራሱ ሆኖ ሳለ ነገር ግን በሰላማዊ መንገድ አደባባይ ወጥተው የፍትሕ ጥያቄ ያቀረቡትን ዜጎች ድምፃቸውን በማፈን እየወሰደ ያለው ጭካኔ የተሞላበት ግድያ፣ የማሰርና የመመንጠር እርምጃ አጥብቀን እናወግዛለን። ድርጊቱንም በአስቸኳይ እንዲቆምና በዚሁ ሳቢያ እስር ቤት የታጎሩትን የህሊና እስረኞች እንዲፈቱ እንጠይቃለን። ለተፈጠረው ችግርና ለተፈፀመው ግድያም በገለልተኛ አካል ተጣርቶ በደለኞቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን።

4. መንግስት ለሀገርና ለህዝብ ድህንነት ሲባልና ለራሱ ህልውናም ሲል የሰላም እጁን በመዘርጋት የህዝቡን ድምፅ የሚስተናገድበት ነፃና ገለልተኛ የፍትሕና የዴሞክራሲ ተቋማትን በመዘርጋት፣ ህዝቡ በሕገ መንግስቱ የሰፈሩትን ሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በመጠቀም መፃኢ ዕድሉን የሚወስንበት ነፃ የምርጫ ስርዓትን በማቋቋም: የፓለቲካ ምሕዳሩን ከላይ እስከ ታች በማስፋት: በአጠቃላይ ኢሕአዴግንም ጨምሮ የለውጡን አጋር የሚሆንበትን ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ለማደረግ የሚያስችል የተመቻቸ የፓለቲካ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈጥር አጥብቀን እንጠይቃለን።
5. መከላኪያ ሰራዊት የገባኸው ቃል ኪዳን ከሁሉም ገለልተኛና ነፃ ሆነህ ለሕገ መንግስቱ፣ ለሀገር ሉዓላዊነትና ለህዝብ ልዕልና ታማኝና ዘብ በመሆን የዜጎችን ድህንነት በእኩል ለመጠበቅ ነው። የሚከፈልህን ደመወዝም ሆነ የታጠቅከውን መሳሪያ ከጥቂት መሪዎች ኪስ የምታገኘው ጉርሻና ስጦታ ሳይሆን የጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ አንጡራ ሀብት ነው። ስለሆነም አንተ ከህዝብ አብራክ የወጣኸው የኢትዮጵያ ወታደር እየከሰመ በመሄድ ላይ የሚገኘውን አምባ ገነን ስርዓትና በተለይም በፍቅረ ንዋይ ታውረው ሐቁን ማየት የሳናቸውና መንገዱን ጠፍቶባቸው በመደነባበር ላይ የሚገኙትን መሪዎች ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል አፈ ሙዙን በጭቁኑ ህዝብ ላይ ከማነጣጠር ይልቅ ከህዝቡ ጋር ወግነህ የለውጡን አጋር እንድትሆን ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

6. ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች፣ ሲቢክ ማሕበረ ሰቦች፣ ምሁራን፣ የሀይማኖት አባቶችና የሚዲያ ባለሙያዎች በሙሉ!! በመካከላችን በብዙ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ መለስተኛ ልዩነት መኖር ባህሪያዊ ነው። ነገር ግን በእናት ሀገርና በህዝብ ህልውናና ደህንነት ላይ ግን ልዩነት ሊኖረን ፍፁም አይገባም። ስለሆነም ጥቃቅን ልዩነቶቻችንና ቅራኔዎችን ወደጎን በመተው ከሁሉም በላይ "<u>የሀገርንና የህዝብን ደህንነትና አንድነት ይቅደም</u> " በሚል የሀገር አድን የጋራ መፈክር ዙሪያ ተሰባስበን የአባቶቻችንን ወኔና ጀግንነት ዳግም በማደስ ለእናት ሀገራችን ትንሳኤ አብረን ዘብ እንድንቆም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

7. መንግስትንና ህዝብን በውል ለይቶ ማየት ያቃታቸውን ቡድኖችና ግለ መሪዎች በጉዳዩ ላይ ምንም በሌለበትና ለራሱ በህወሓትና በሻዕቢያ በሁለት አለንጋ እየተገረፈ በባርነት ስር እየማቀቀ የሚገኘውን የትግራይ ህዝብ ከወንለኛ መሪዎች ጋር ደምረው በጅምላ በመጥላት የህዝቡን ስሜትንና ክብርን የሚነካ ተግባር ሲፈፅሙ ይገኛሉ። በመሆኑም ለረጅም ዘመናት አብሮ ተፋቅሮና ተዋልዶ በኖረው ወንድማማች ህዝብ መካከል ሆን ተብሎ በዘር ጥላቻ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን በመገፋፋት አላስፈላጊ ግጭትና የእርስ በርስ መናቆር ለመፍጠር የሚደረገውን ማንኛውም ሕገ ወጥ ድርጊት አጥብቀን እናወግዛለን። አንዳንድ የመንግስት አካላትም ሆኑ ሌሎች ግለ ሰቦችና ቡድኖች ወጣቱን ትውልድ የሀገርንና የወገንን ፍቅር ተላብሶ በመቻቻል አብሮ መኖርን ከማስተማር ይልቅ ጥላቻን በመስበክ በገዛ ወገኑ ላይ እንዲዘምት ከማድረግ እንዲታቀቡ አበክረን እንጠይቃለን።

8. የኢትዮጵያ ህዝብ! ባንተ ላይ ነጋ ጠባ ሲካሄዱት የቆዩትን አደናጋሪና ከፋፋይ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ በምንም ሳትበገር፣ መንግስታትና መሪዎች አላፊ ሀገርና ህዝብ ግን ነባሪ መሆናቸውን በፅናት በማመን ላሳየኸው ትዕግስትን: ጨዋነትንና ሃላፊነትን የተሞላበት አኩሪ ተግባርና ባህል ምስጋናችንንና አንድናቆታችንን ስንገልፅ ታላቅ ኩራት ይሰማናል። ስለሆነም ዛሬም እንደትላንቱ ዓለም ያደነቀውን የአትንኩኝ ባይነትህን: እንግዳ ተቀባይ ተምሳሌነትህንና የአንድነት ቃል ኪዳንህን ጠብቀህ ከስርዓቱ ጭቆናና አፈና ለመላቀቅ በምታደርገው ህዝባዊ ተጋድሎ ላይ እኛም እስከመጨረሻ ከጎንህ የምንቆም መሆናችንን በልበ ሙሉነት ለመግለፅ እንወዳለን።

እግዚአብሄር የሀገራችንን ሰላምና አንድነት ይጠብቅ